የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ – ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 49
ADDIS ABABA– 22nd April, 1999

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፰/፲፱፻፺፩ ዓ.ም
የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ)
አዋጅ ...................................... ገጽ ፲፻፳፩

CONTENTS

Proclamation No. 168/1999
Investment (Amendment)
Proclamation ...................................... Page 1021

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፰/፲፱፻፺፩
## የኢንቨስትመንት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢንቨስትመንት አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፰/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፹፰ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፡

፩· የአዋጁ አንቀጽ ፯ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፯ ተተክቷል፡

"፯· ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ስለሚካሄድ ኢንቨስትመንት

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማንኛውንም ባለሀብት ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ኢንቨስት ለማድረግ የሚያቀርበውን የፕሮጀክት ሃሣብ ይቀበላል፡ ለመንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፡ ሲፈቀድም በቅንጅት ተሳታፊ የሚሆነውን የልማት ድርጅት ይሰይማል።"

## PROCLAMATION NO. 168/1999
## A PROCLAMATION TO AMEND THE INVESTMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Investment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short title*

   This Proclamation may be cited as the "Investment (Amendment) Proclamation No. 168/1999."

2. *Amendment*

   The Investment Proclamation No. 37/1996 (as amended) is hereby further amended as follows:

   1) Article 7 of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Article '7':

      *"7" Investments to be Undertaken in Partnership with the Government*

      The Supervising Authority of Public Enterprises shall receive and evaluate projects proposals submitted by any investor intending to invest in partnership with the Government; submit same to the Government for decision and, upon approval, designate a public enterprise to invest as partner in the joint investment.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price ብር 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O. Box 80,001

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፰ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፰ ተተክቷል፣

"፰. <u>ለውጭ ባለሀብቶች የተፈቀዱ የሥራ መስኮች</u>

፩. በዚህ አዋጅ መሠረት ለመንግሥት፣ ለኢትዮጵያ ውያን ወይም ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ወይም ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ብቻ ለሚካሄዱ ኢንቨስት መንቶች ተለይተው ከተከለሉት በስተቀር ሌሎች የሥራ መስኮች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ይሆናሉ።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው እንደተ ጠበቀ ሆኖ ፣ የውጭ ባለሀብት ከሀገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት ኢንቨስት የሚያደርግ ከሆነ የሀገር ውስጥ ባለሀብት የካፒታል ተዋጽኦ መጠን ከ፪ በመቶ (ሁለት ፐርሰንት) ያነሰ አይሆንም።"

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

*2) Article 8 of the proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Article '8'.*

*"8" Areas of Investment open for Foreign Investors*

1/ All areas of Investment, other than those exclusively reserved under this proclamation for the Government, Ethiopian nationals or domestic investors or for joint investments with the Government, shall be open for foreign investors.

2/ Without prejudice to Sub Article (1) of this Article, the equity share of the domestic partners in a joint investment shall not be less than two-percent (2%).

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 22nd day of April, 1999.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of April, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE